# ACPS Express 4/21/2023: የኤፕሪል የአጋር እና የበጎ ፈቃደኛ ዋና ዋና ነገሮች — UpCycle Creative Reuse Center

## የኤፕሪል የአጋር እና የበጎ ፈቃደኛ ዋና ዋና ነገር፡- UpCycle Creative Reuse Center



በኤፕሪል 22፣ 2023 ላይ የሚኖረውን የመሬት ቀንን በማስመልከት፣ Alexandria City Public Schools (ACPS) ከUpCycle Creative Reuse Center ጋር ያለውን አጋርነት በዚህ ወር ያከብራል። UpCycle በፈጠራዊ የመሳሪያዎች ዳግም አጠቃቀም በኩል ስነጥበብን እና አካባቢን ያገናኛል። ትርፋማ ያልሆኑት ፕሮግራሞች እና ዝግጅቶች ለACPS ተማሪዎች ለሆነ ወደፊት አስፈላጊ የሆኑ ዘላቂ እሴቶችን ያሰርጻል። ላለፉት አምስት አመታት፣ UpCycle በ10 የACPS ት/ቤቶች እና የመዝናኛ ማዕከላት ከት/ቤት ውጪ ጊዜ ፕሮግራሚንግን ሲመራ ቆይቷል። በተጨማሪም UpCycle በመሳሪያዎቹ ማዕከል የት/ቤት ቡድኖችን አዘጋጅቷል እንዲሁም በአመታቱ ውስጥ ከበርካታ የACPS አስተማሪዎች ጋር ሰርቷል።

"መሳሪያዎችን ከመጣል ይልቅ እንዴት ሊቀመጡ እንደሚችሉ እንዲሁም ፈጠራዊ በሆኑ መንገዶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ለማሳየት እንወዳለን" ይላሉ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆኑት Director Theresa። "የፈጠራ ዳግም አጠቃቀም ከጊዜ ወደጊዜ ከፍ እያሉ በመጡት የቆሻሻ መሙላቶች፣ ከመጠን በላይ የሆነ ምርት እና የተፈጥሮ ሃብቶች መመናመን ውጤታማ የሆነ ምላሽ እንደሆነ እናምናለን። ሁሉንም አይነት ነገሮች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ዳግም ማሰላሰል ነው።"

Upcycle እያንዳንዱ ሰው በስነጥበብ እና በሌላ ክፍት በሆኑ ነገሮች የአሰሳ ተሞክሮዎች በኩል ሊገለጡ የሚችሉ እይታዎች እና ሃሳቦች እንዳሉት በሚያምነው በReggio Emilia የመማር አካሄድ ፍልስፍና የተመሰረተ ነው። የመተባበር እሴት በእያንዳንዱ የUpCycle አቅርቦቶች ላይ ይንጸባረቃል።



የUpCycle የምልከታዊ ፕሮግራም የሆነው Tinker Time በእቃዎች ማእከሉ ለቤተሰቦች በነጻ ከሚያቀርበው ስፖንሰርሺፕ ጋር በዚህ ወር ዳግም ይከፈታል። ምንም እንኳን 12 እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆችን ጋር አንድ አዋቂ ሰው አብሮ መሆን ቢኖርበትም፣ ይህ በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ላሉት መዋቅራዊ ያልሆነ ክፍት የአሰሳ ጊዜ ነው። በማዕከሉ፣ UpCycle በተጨማሪ ለወጣቶች እና

አዋቂዎች ወርክሾፖችን ያቅርባል እንዲሁም እድሜያቸው ከ3 ½ እስከ 10 አመት ለሆናቸው ቀጣይ የሰመር ካምፕ ያዘጋጃል። በተጨማሪም የመሳሪያዎች ማእከል የት/ቤት ቡድኖችን ለመስክ ጉዞዎች ያመቻቻል።

እንደ Esterlund ከሆነ፣ ጎብኝዎች ወደ UpCycle የሚደርጉት ጉዞ የመፍጠር አቅማቸውን እንደሚያልቀው ይናገራሉ። ፈጠራ ጥልቅ ግንዛቤን፣ ብልህነትን እና ፈጠራን እንደሚያጠናክር አጽንኦት ሰጥታለች። “ልጆች በፈጠራዊ ሂደቶች ውስጥ ሲሳተፉ፣ ችግሮችን መፍታት ይማራሉ እና በተለዋዋጭነት ያስባሉ ይህም በት/ቤት እና በህይወት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆን ወደሚያደርጓቸው የህይወት ክህሎቶች ይመራቸዋል።” Esterlund ተናገረች። “ከዚህም በተጨማሪ፣ ምርምር እንደሚያሳየው ከሆነ ፈጠራዊ አገላለጽ በአእምሮ ጤና ላይ አዎንታዊ ውጤት አለው፣ ጭንቀትን ይቀንሳል እንዲሁም ጠቅላላ ደህንነትን ያሻሽላል።”

UpCycle ባለፈው አመት ከ30,000 በላይ ፓውንዶችን ልገሳ አድርጓል ይህም በቆሻሻ ውስጥ ሊጣሉ የሚችሉ እና የሚቃጠሉ ቁሶችን ቆጥቧል። ከወረቀት እስከ ክር፣ ጨርቆች እና ቀለም ድረስ UpCycle ለእጅ ስራዎች እና ለት/ቤት ፕሮጀክቶች በርካታ ነገሮች አሉት። “የኩባያ ክዳኖች፣ ፕላስቲክ ወይም የብረት ቁርጥራጮች፣ የእንጨት ቁራጮች፣ መያዣዎች እና  ሁሉም አይነት ያልተለመዱ እና የማይጠበቁ መሳሪያዎች ምናባዊ አስተሳሰብን ለማነሳሳት እና  እነዚህን የመሳሰሉ የእለት ተእለት እቃዎችን ባይጥሉ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ሰዎች እንዲገነዘቡ ለማስቻል ትክክለኛ ነገሮች ናቸው።” ትላለች Esterland።

ቅዳሜ ኤፕሪል 22፣ 2023 ባለው የመሬት ቀን አከባበር፣ UpCycle  ነጻ የሆነ የመጣል እንቅስቃሴዎችን ከ10a.m. እስከ 4p.m. ድረስ ያቀርባል፣ ይህም የማህበረሰብ አባላት ዳግም የተነደፉ ቦታዎችን የማየት እድል ይሰጣቸዋል። እቃዎቹን ለመለገስ፣ የthe UpCycle ድረገጽን ይጎብኙ እና ቀጠሮ ያስይዙ።

## የAlexandria City School ቦርድ የባለድርሻ አካላት የዳሰሳ ጥናት በኤፕሪል 26፣ 2023 ይዘጋል



የ Alexandria City School ቦርድ ማህበረሰባችንን የሚያገለግሉ የት/ቤት ቦርድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉ ቁልፍ ችግሮች የዳሰሳ ጥናት ውስጥ ሁሉም የባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ይጠይቃል። ይህ የዳሰሳ ጥናት በበርካታ ቋንቋዎች ኦንላየን ላይ ይገኛል፣ እስከ ኤፕሪል 26፣ 2023 11:59 p.m. ድረስ ክፍት ነው።

በቅርብ ወራት ውስጥ፣ ቦርዱ የት/ቤት ማህበረሰብን ፍላጎቶች በተሻለ መልኩ ለማገልገል የት/ቤት ቦርዱን መዋቅር ዳግም ለመቅረጽ መንገድ ጀምሯል። የተዘበራረቀ ዘመን፣ የስራ ዘመን ርዝማኔ እና የቦርድ አባላት ቁጥር በማካተት በቦርድ አባል ምርጫዎች ላይ ለውጦች እንዲኖሩ አስቧል።

ከግምት ውስጥ የገባ አንደኛው ዋነኛ አካል እና ማህበረሰቡ ከለመደው ለየት የሚለው “የተዘበራረቀ የስራ ዘመን” የሚለውን ነው። ይህ ሲተረጎም የት/ቤት ቦርድ አባላት በተለያዩ አመታት በመመረጥ ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከሚሆኑ ይልቅ የት/ቤት ቦርድ አገልግሎትን ጊዜያቸውን የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት ጊዜ በተለያዩ ጊዜያት ማድረግ ነው። በአሁኑ ጊዜ፣ ዘጠኙም ሁሉም የት/ቤት ቦርድ አባላት ጊዜያቸውን በተመሳሳይ ሰዓት የሚጨርሱ ሲሆን በተመሳሳይ አመት በተመሳሳይ ምርጫ ውስጥ ይመረጣሉ። የተዘበራረቀ የስራ ዘመን አባላት በተለያዩ ዓመታት ውስጥ አባላት እንዲመረጡ ያስችላቸዋል፣ ይህም ቦርዱ ቀደም ሲል ሲያገለግሉ

የቆዩትን አንዳንድ አባላቱን እንዲይዝ ያደርጋል፤ ይህ ተከታታይነትን እና የተቋም እውቀትን ይደግፋል። በተጨማሪም፣ አዳዲስ አባላትን ወደ ክፍሉ ስራ በሚመደቡበት ጊዜ የክፍሉን ስራ አሟልቶ ለማቆየት ቀላል ነው።

ይህንን ሂደት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህንን አቅርቦት ይገምግሙ ወይም ይህንን የፌብሩዋሪ 9፣ 2023 በት/ቤት ቦርድ የስራ ክፍለ ጊዜ ቪዲዮ ይመልከቱ። እንዲሁም፣ የት/ቤት ቦርዱ ሐሙስ ኤፕሪል 20፣ 2023 ላይ ከ6:30 p.m. ጀምሮ በቦርድ ስብሰባው ላይ በዚህ ርዕስ ህዝባዊ ችሎትን አድርጓል።

ቦርዱ በዚህ ሂደት ውስጥ የባለድርሻ አካላት ድምጽ በጣም አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ላይ ይሆናል እንዲሁም ቦርዱ እርምጃዎችን ከመውሰዱ አስቀድሞ የማህበረሰብ አባላት የዳሰሳ ጥናቱን እንዲያጠናቅቁ እና ግብዓታቸውን እስከ ኤፕሪል 26፣ 2023 እንዲያስገቡ ይጋብዛል። እነዚህ ለውጦች የክንውኖችን ቀጣይነት፣ የነዋሪ ውክልናን፣ ተጠያቂነትን እና የምርጫዎችን ጊዜ ላይ ተጽእኖ ሊያሳርፍ ይችላል። የባለድርሻ አካላት ግብአት በእነዚህ እያንዳንዱ አካባቢዎች ውሳኔዎችን ገፅታ ይሰጣል። ግብረመልሱን ላቀረባችሁ ሰዎች በሙሉ እናመሰግናለን።

## አዲስ ክፍት፡- ለ2023-24 የትምህርት አመት የመዋእለ ህጻናት ምዝገባ



Alexandria City Public Schools (ACPS) ለ2023-24 የትምህርት አመት የመዋዕለ ህጻናት ምዝገባን አሁን ላይ ጀምሯል እና ሁሉንም ሰው የመዋዕለ ህጻናት ተማሪዎቻቸውን አስቀድመው እንዲያስመዘግቡ ያበረታታል። ቤተሰቦች ልጃቸው የእድሜ መስፈርቶችን እንደሚያሟላ ለማረጋገጥ እና በቀጣዩ የትምህርት አመት ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ለማወቅ የምዝገባ የድር ገጾችን መጠቀም ይችላሉ። የመገኘት ዞን አመልካች መሳሪያ ቤተሰቦች የት/ቤት ዞኖቻቸውን እንዲያገኙ ይረዳል።

በተጨማሪ፣ ቤተሰቦች ስለትምህርት ቤታቸው በበለጠ እንዲያውቁ ለማድረግ ACPS የመዋዕለ ህጻናት ክፍት ቤቶችን ያዘጋጃል። ስለት/ቤቱ የመዋእለ ህጻናት ክፍት ቤት ዝርዝሮችን ለማግኘት የት/ቤትዎን ድረ ገጽ ይጎብኙ፤ እንዲሁም፣ የመዋእለ ህጻናት ምዝገባ መረጃ በACPS ድረገጽ ላይ ይገኛል። ቤተሰቦች የመዋእ ህጻናት ተማሪዎቻቸውን ለማስመዝገብ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚገኘውን የ2023-24 የትምህርት አመት የኦንላይን ላይ የተማሪ ምዝገባ ቅጽን መጠቀም ይገባቸዋል። ቀጣዩ እርምጃ መቼ ላይ ለመጎብኘት እንደሚችሉ እና የምዝገባ ሂደቱን ለማጠናቀቅ ሁሉንም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በአካል ማረጋገጫ ለማቅረብ እንደሚቻል ት/ቤቱ ጋር መደወል ወይም የት/ቤት ሬጅስትራርን ማነጋገር ነው።

በ2023-24 የመዋዕለ ህጻናት ተማሪዎች ያሏቸው ቤተሰቦች ACPS ለሚመጡ የመዋዕለ ህጻናት ተማሪዎች “Step Up to Kindergarten” ተብሎ በሚጠራው የግማሽ ቀን ግንዛቤ ማስጨበጫ ላይ በሚኖረው ዝግጅት ላይ አርብ ኦገስት 18፣ 2023ን በማስታወስ ቀኑን ለመያዝ ይፈልጋሉ። ይፋዊ የትምህርት አመቱ ከመጀመርዱ በፊት ያለው የት/ቤት ተሞክሮ ትውውቅ የመዋእለ ህጻናት ተማሪዎችን ከት/ቤቶቻቸው፣ ከክፍሎቻቸው እና ከአስተማሪዎቻቸው ጋር እንዲተዋወቁ በማድረግ በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ቀን ላይ የበለጠ ምቾት እንዲሰማቸው ያደርጋል።

## ACPS ሃገራዊ የአረብ ቅርስ ወርን ያከብራል




ሃገራዊ የአረብ አሜሪካዊ የቅርስ ወር አረብ አሜሪካዊያን ለሃገራችን እና ማህበረሰባችን ያደረጓቸውን ሊለኩ የማይችሉ አስተዋጽኦዎች ማክበር ነው። ምንም እንኳን አረብ አሜሪካዊያን በሁሉም U.S. ስቴቶች ውስጥ ቢኖሩም፣ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በ10 ስቴቶች ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ ቨርጂኒያ አንደኛው ስቴት ነው። የአረብ አሜሪካ ተቋም በመካከለኛው ምስራቅ እና በሰሜን አፍሪካ የሚገኙት 22 ሀገራትን የዘር ሀረጋት ኢራቅ፣ ሊባኖስ፣ሳውዲ አረቢያ፣ሶሪያ፣ የመን እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶችን በማካተት አሳይቷል። Alexandria City Public Schools (ACPS) አረብኛ ቤት ውስጥ የሚነገረው ቋንቋ መሆኑን የዘረዘሩ ከ500 በላይ ከpre-K-12 ተማሪዎች አሉት።

አረብኛ ተናጋሪ ሰራተኞች ከክፍል ውስጥ ጀምረው እስከ ት/ቤት አስተዳደር ድረስ ክፍሉን ይደግፋሉ። በተጨማሪም፣ የቤተሰብ ግንኙነቶች በት/ቤታችን እና በሚያገለግሏቸው የተለያዩ ቋንቋ የሚናገሩ ቤተሰቦች መካከል እንደ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰብ አገናኞች፣ ራሱን የቻለ የአረብ ቤተሰብ አገናኝ የስራ መደብን ጨምሮ፣ ፕሮግራሚንግ ያዘጋጃሉ፣ በተዳርሶ ላይ ይሳተፋሉ እና ቤተሰቦችን ወደ ት/ቤት ስርዓት መሸጋገራቸውን ከሚያቃልሉ ግብዓቶች እና ድጋፎች ጋር ያገናኛሉ። ለልጆቻቸው እና ለማህበረሰቦቻቸው ተሟጋቾች ሆነው ለመስራት የራስ መተማመን እንዲሰማቸው ከሁሉም የቋንቋ እና የባህል መሰረቶች የመጡ ቤተሰቦች እና እንክካቤ ሰጪዎችን እንዲሁ ያጎለብታሉ።

በኤፕሪል ወድ ሃገር አቀፍ የአረብ አሜሪካዊያን የቅርስ ወርን በምናስብበት ጊዜ፣ ባህላዊ ተቋማት፣ የት/ቤት ክፍሎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ የግዛት የህግ አካላት እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች የአረብ ማህበረሰብ ባለጸጋ ቅርስ እና በርካታ የማህበረሰብ አስተዋጽኦዎችን ያከብራሉ። ከቨርጂኒያ ገዢ Glenn Youngkin የሚሰጥ [የእውቅና ሰርተፍኬት]() የአረብ አሜሪካዊ የቅርስ ወር የእኛን ኢኮኖሚ፣ ባህል እና ማህበረሰቦች የሚያጠናክሩ ክህሎቶችን እና አስተዋጽኦዎች ያሏቸው ከ100,000 በላይ አረብ አሜሪካዊያንን የሚያወድስ እድል ነው፡፡

## የቀን መቁጠሪያዎ ላይ ምልክት ያድርጉ፡- Spring2ACTion ለኤፕሪል 26፣ 2023 መርሃግብር ተይዞለታል




የAlexandria አለም አቀፍ የመስጠት ቀን የሆነው Spring2ACTion ሊደርስ ቀናት ብቻ ቀርተውታል! ለAlexandria በACT የሚቀርበው የዚህ አመት Spring2ACTion ለእሮብ ኤፕሪል 26 መርሃግብር ተይዞለታል። የ24 ሰአቱ የኦንላየን ላይ ዝግጅት

ማህበረሰባችንን የሚረዱ ለጋሾች እስከ ትርፋማ ያልሆኑ ድርጅቶች ያገናኛል። ቅድሚያ መስጠት የተጀመረው በኤፕሪል 12፣ 2023 ነው።

በዘመቻው አላይ በሚኖራቸው ተሳትፎ ባንድ፣ ኮራል፣ ኦርኬስትራ እና ስፖርቶችን የሚደግፉ በርካታ የAlexandria City High School (ACHS) የማጠናከሪያ ክለቦች ለፕሮግራሞቻቸው ገንዘብ ማሰባሰቢያ መንገዶችን እየፈለጉ ነው። በAlexandria Council of PTAs (PTAC) በAlexandria City Public Schools (ACPS) የቤተሰብን ፍትሃዊነትን ለማሳደግ ገንዘብ ለማሰባሰብ በዝግጅቱ ላይ እየተሳተፈ ነው የእርስዎ ልገሳ በአሌክሳንደርያ በጣም ተጋላጭ ልጆችን በሚያገለግሉ ት/ቤቶች ውስጥ ለቤተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል።

“ይህ አመት PTAC፣ ፍትሃዊነትን ለመፍጠር በመላው ክፍሎች የመስክ ጉብኝት፣ በTitle I ት/ቤቶቻችን የቤተሰብ ተሳትፎን የመጨመር፣ የአባልነት ዘመቻዎቻቸውን መደገፍ እና የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የመስጠት ጥረቶቻችን ላይ ትኩረት ያደርጋል” ይላሉ የPTAC ፕሬዚዳንት የሆኑት Missy Santoro Estabrook።

የት/ቤት ክፍል የPTA አሃዶች የራሳቸውን የተወሰኑ ግቦች ለመደገፍ ራሳቸውን ችለው ለዝግጅቶቹ ተመዝግበዋል። “እንደ Spring2ACTion ያሉ ዘመቻዎችን ማካሄድ ከቤተሰቦቻችን ጋር ያለውን ግንኙነት መልካም እንዲሆን፣ ከማህበረሰባችን አጋሮች ጋር ትብብርን የተሻለ በማድረግ እና ለእያንዳንዱ ልጅ ድጋፍ ሆነን የምንናገርባቸውን የተሟጋችነት ጥረቶችን ለማሻሻል በገንዘብ ይረዳናል፣” ብለው ያስገነዝባሉ Estabrook። "ለታታሪ ክፍሎቻችን እና ጥረታችንን ለሚደግፉት አብዛኛው ማህበረሰብ በጣም አመስጋኞች ነን!"

Spring2ACTion 13ኛውን አመት እያከበረ ነው። ACT ለAlexandria’s የ 2023 ግብ 10,000 ለጋሾችን እና 165 ተሳታፊ ድርጅቶችን በማድረግ ከ$2.5 ሚሊየን በላይ መሰብሰብ ነው።

## 15,000 የACPS በጎ ፈቃደኞች ማመስገን




በAlexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ ያሉት በጎ ፈቃደኞቻችን በኤፕሪል ወር ውስጥ በሃገራዊ የበጎ ፈቃደኝነት ወር እና የበጎ ፈቃደኛ ሳምንት ወቅት፣ ከኤፕሪል 17-21 ተከብሯል። የእኛ አስደናቂ በጎ ፈቃደኞቻችን ለት/ቤቱ ክፍል፣ ለተናጥል ት/ቤቶች እና — ከሁሉም በላይ — ለተማሪዎቻችን ተጨማሪ ድጋፍን ያቀርባሉ።

በጎ ፈቃደኞች በክፍል ውስጥ እና በት/ቤት ክፍል ሁሉ ጊዜያቸውን በበርካታ መንገዶች ይሰጣሉ። ድጋፋቸው ሁሉም ተማሪዎች እንዲበለጸጉ በማነቃቃት ግብዓቶችን በማቅረብ በACPS 2025 ፍትሃዊነት ለሁሉም ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ውስጥ ካለው የፍትሃዊነት እና መጎልበት ጭብጦች ጋር አብረው ይሄዳሉ። በACPS የሚገኙ ወደ 15,000 የሚጠጉ በጎ ፈቃደኞች በመስክ ጉዞዎች፣ በማጠናከሪያ ትምህርት፣ በመካሪነት፣ በአሰልጣኝነት እና ለተማሪው ስኬት ወሳኝ በሆኑ በሌሎች አካባቢዎ ላይ እገዛ አድርገዋል።

“ሁሉንም የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች — ይህም በእኛ አጋሮች፣ እና የህበረሰብ አባላት ወይም የቤተሰብ አባላት የሆኑ — የሲቪክ ተሳትፎን ያነቃቁ እና የህይወት ዘመን ተማሪዎችን ያበረታቱትን ላመሰግን እወዳለሁ”፣ ብለዋል የማህበረሰብ አጋሮች እና የተሳትፎ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት Kurt Huffman። “የእያንዳንዱ ተማሪን ስኬትን በእውነት ለማግኘት፣ ሁሉም የመማር ስነምህዳር አካላት እርስ

በርስ ተጣጥመው በመስራት ልዩ የሆኑ አስተዋጽኦዎቻቸውን ማስታጠቅ የእኛ ታዳጊ ልጆች ከፍተኛ የብቃት ደረጃቸው ላይ እንዲደርሱ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ጠንካራ የሆነ እምነት አለኝ። በጎ ፈቃደኞች በእርግጠኝነት ለስኬት አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንደኞቹ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ይፋዊ የACPS ማህበረሰብ አጋሮቻችን በመላው አሌክሳንድሪያ በሚገኙ በጎ ፈቃደኞች የሚያስደንቅ አስተዋጾ ማለትም — ጊዜ፣ ችሎታ፣ እውቀት — ላይ ስለሚተማመኑ የት/ቤት ክፍላችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አላቸው።

የበጎ ፈቃደኛ ድጋፍ በFamily and Community Engagement (FACE) ማእከል በኩል ባሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍን የሚያካትት ሲሆን የትምህርት ተሞክሮን እና የተማሪዎችን አካዳሚክ ስኬት ለማጎልበት ያግዛል። አንዳንዶቹ የእኛ የ ACPS በጎ ፈቃደኞችን እንደ Alexandria Tutoring Consortium ከመሳሰሉት ጋር በጋራ በመስራት በጎ ፈቃደኞች ተጨማሪ የንባብ ድጋፍ ለሚፈልጉ የመዋእለ ህጻናት እና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ጋር በጋራ እንዲሰሩ ያሰለጥናሉ። ተማሪዎች በጎ ፈቃደኞችን በት/ቤት ውስጥ ሲመለከቱ፣ የማህበረሰቡ አባላት ለትምህርት ዋጋ እንደሚሰጡ እና ስለእነርሱ እንደሚጨነቁ ያያሉ። እና በጎ ፈቃደኞች ዋጋ ሲሰጣቸው፣ በአካባቢያቸው ባሉ ት/ቤቶች ያላቸውን ፍላጎት ያጋራሉ።

“በጎ ፈቃደኞቻችንን እንወዳቸዋለን” ይላሉ የFACE በጎ ፈቃደኛ ስፔሻሊስት የሆኑት Angela Houghton አጽንኦት ሰጥተው እንደተናገሩት። “እንደ ተማሪዎቻችን የማክሮ ሲስተም አንድ አካል፣ የእርስዎን ጊዜ ለሌሎች የማሰብ እርምጃ፣ ለተማሪዎቻችን እና ለሰራተኞቻችን የጥንካሬ ምንጭ እና በማንኛዉም አይነት አስፈላጊ መንገድ እነርሱ እንዲሳካላቸው ማገዝ አድርገን በትክክል ለይተነዋል።”

ከACPS ጋር ያሉ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎቶች ከት/ቤት ት/ቤት ይለያያሉ። ለአንዳንድ ግለሰቦች፣ በጎ ፈቃደኝነት የት/ቤት ዝግጅቶችን በማቀድ ወይም በማዘጋጀት ማገዝ ወይም ት/ቤታችንን እና ተማሪዎቻችንን ለመጥቀም በParent-Teacher Association (PTA) የክፍል እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍን ሊያካትት ይችላል። የት/ቤቱ ክፍል በትምህርት አመቱ ሁሉ በመሳተፍ ተማሪዎቻችንን ለረዱ ቤተሰቦቻችን፣ የማህበረሰብ አባላት እና አጋር ድርጅቶች ምስጋናውን ያቀርባል። ለሰጡት አገልግሎት ትልቅ ምስጋና እናቀርባለን።

ለመሳተፍ ፍላጎት አለዎት? ከACPS የበጎ ፈቃደኛ ስፔሻሊስት ጋር የስብሰባ መርኃግብር የሚያወጡበት እና የበጎ ፈቃደኛ ማመልከቻን የሚሞሉበትን የበጎ ፈቃደኛ የድር ገጻችንን በመጎብኘት የበለጠ ይወቁ።

## “የወደፊትዎን ዛሬ” የቅዳሜ ስልጠና ዝግጅት ለኤፕሪል 29፣ 2023 መርሃግብር ተይዞለታል



ቅዳሜ ኤፕሪል 29፣ 2023 ላይ የAlexandria City Public Schools (ACPS) ከ8-12ኛ ክፍል ላሉ ጥቁር/አፍሪካዊ አሜሪካውያን ወንዶች የተዘጋጀውን “የወደፊትዎን ዛሬ” የተባለውን የመጀመሪያውን የቅዳሜ ዝግጅቱን ያስተናግዳል። የ ACPS ስትራቴጂያዊ እቅድ ትኩረት የሆነውን “ፍትሃዊነት ለሁሉም” ለመጠበቅ፣ ይህ ዝግጅት የጥቁር ወንድ ወጣቶችን ልዩ ፍላጎቶች ማወቅ እና ማሰልጠን ላይ ትኩረት ያደርጋል። የእኛ ዳታ እንዳሳየው ይህ የተማሪዎች ቡድን በስነምግባር ውጤቶች፣ መያዞች/መታሰሮች እና የአካዳሚክ አለመመጣጠን ላይ ከመጠን በላይ ተወክሏል። ጠንካራ የስልጠና ግንኙነቶችን በማጎልበት፣ አንዳንድ ጥቁር ወንድ ወጣቶች የሚያጋጥሟቸው እንቅፋቶች ሊቀንሱ ይችላሉ እናም የስኬት አቅማቸውን በማበረታታት የማህበረሰቦች፣ የቤተሰቦች እና የባህሎች ጥንካሬን ለማጠናከር ሊያገለግሉ ይችላሉ።

“የወደፊትዎን ዛሬ” የሚለው ዝግጅት በFrancis C. Hammond Middle School (4646 Seminary Road) ከ 9 a.m. እስከ 1 p.m. ድረስ ይካሄዳል። የቀኑ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች የሚያካትቱት፡-

- ቁርስ እና የአቻ ትውውቆች።
- ከጊዜያዊ የበላይ ተቆጣጣሪ እና የት/ቤት ቦርድ አባላት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልክት።
- ብልህ የሆኑ ውሳኔዎችን ማድረግ፣ ህጉን መገንዘብ እና እንቅፋቶችን ማለፍ በሚሉት ላይ ከጥቁር ወንድ አሰልጣኞች የሚሰሙ እድሎች።
- የፋይናንሻል እውቀት ክፍል
- ስነምግባር ክፍል (ምሳን የሚያካትት)።

ይህ ዝግጅት የእኛን የጥቁር/የአፍሪካ አሜሪካዊያን ወንዶችን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የተነደፈ ነው፣ ይሁን እንጂ ከ8ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ለመመዝገብ ይችላሉ። ተማሪዎችዎ በዚህ ዝግጅት ላይ እንዲመዘገብ ፍላጎት ካለዎት፣ እባክዎ የኦንላይን የምዝገባ ቅጽን ያጠናቅቁ።

## የACPS የሰመር ትምህርት ምዝገባ አሁን ክፍት ነው




Alexandria City Public Schools (ACPS) ለሁሉም የአሁን ከPreK-8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሰመር ትምህርት ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን እየቀጠልን መሆናችንን ስናሳውቅ በደስታ ነው። ሌላ የተግባር የሰመር ማበልጸጊያ ተሞክሮን ስናቀርብ እና ሁሉም የአሁን የACPS ከPreK-8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ነጻ የሰመር ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ እንዲመዘገቡ ስንጋብዝ በደስታ ነው።

ለእነዚህ ፕሮግራሞች ምዝገባ ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ሲሆን ከአርብ ኤፕሪል 14፣ 2023 8 a.m. ላይ በመጀመር እሁድ ሜይ 14፣ 2023 11:59 p.m. ላይ ይዘጋል። በሰመር ትምህርት ልንቀበላቸው የምንችላቸው የተማሪዎች ቁጥር በሰመር ት/ቤት ጣቢያ እና በሰራተኞች አቅም ላይ ስለሚወሰን ቤተሰቦች ቀድመው እንዲያስመዘግቡ አጥብቀን እንበረታታለን። ልጆቻቸው ለሰመር ትምህርት እንዲመዘገቡ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች የACPS የሰመር ትምህርት 2023 የድር ገጽን መጎብኘት አለባቸው። የሰመር ትምህርት 2023 በራሪ ወረቀቶችን በ English፣ Spanish፣ Dari፣ አማርኛ እና አረብኛ ይመልከቱ።

የሰመር ትምህርት ተሞክሮ የሚያተኩረው ከK-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሳይንስ, ቴክኖሎጂ, ምህንድስና እና ሂሳብ (STEM) ላይ እንዲሁም ከ5ኛ እስከ 7ኛ ላሉ ተማሪዎች ደግሞ የሙያ አሰሳ ላይ ያተኩራል። ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በአካል የመገኘት ሙዚቃ እና የቲያትር ካምፖች ውስጥ እንዲሁም የጤና እና PE 9 በሆነው የካንቫስ ኮርስ ኦንላየን ላይ መመዝገብ ይችላሉ። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአካል የሰመር ትምህርት ፕሮግራም የክሬዲት ማስመለሻ ኮርሶች ለሚፈልጉ ተማሪዎች ብቻ ክፍት ይሆናል። አዳዲስ የክሬዲት ኮርሶች በኦንላየን አቅራቢ በኩል ትምህርት ይሰጥባቸዋል።

የACPS የሰመር ትምህርት 2023 ከጁን 26 እስከ ጁላይ 20፣ 2023 ድረስ የአራት ሳምንታት በአካል ተገኝቶ መማርን ያካትታል። ትምህርቱ የሚከናወነው በየሳምንቱ ከሰኞ እስከ ሐሙስ ድረስ ሲሆን አርብ አለት ትምህርት የለም። እንዲሁም ማክሰኞ ጁላይ 4፣ 2023 ትምህርት አይኖርም።

የሰመር ትምህርት ሰዓታት የሚከተሉት ናቸው፡-

- **PreK እና K-4 ክፍሎች** (ወጣት ምሁራንን አካትቶ)፡- ከ8 a.m.-12 p.m.
- **ባለሁለት ቋንቋ፡-** ከ8 a.m.-12 p.m.
- **ከክፍል 5-7፣ የበላሁለት ቋንቋ የሰመር ብሪጅ፣ ቲያትር ካምፕ፡-** 8:45 a.m.-1 p.m.
- **ሁለተኛ ደረጃ እና የሙዚቃ ካምፕ፡-** ከ9:30 a.m.-2:30 (በአካል የሚገኙበት ክፍሎች ብቻ)
- **ሁለተኛ ደረጃ በኦንላየን ላይ፡-** ቀኖቹ እና ሰዓታቱ ተለዋዋጭ እና ተቀያያሪ ናቸው።
- **ልዩ ትምህርት፡-**
  - PreK ክፍሎች፡- ከ9-11 a.m.
  - K-12 እና የድህረ ምረቃ ክፍሎች፡- ከ9 a.m.-1 p.m.

የሚከተሉት ፕሮግራሞች የተለያዩ ቀናት ሊኖሯቸው እንደሚችል እባክዎ ይስታውሱ፡- የሙዚቃ እና የቲያትር ካምፖች፣ የባለሁለት ቋንቋ የሰመር ብሪጅ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኦንላየን ላይ እና የChild Find የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች። ለበለጠ ዝርዝር የፕሮግራም መረጃ እባክዎ የACPS የሰመር ትምህርት 2023ድረ ገጽን ይጎብኙ። ተማሪዎች መጓጓዣ ለማግኘት እስከ ሜይ 14፣ 2023 የመጨረሻ ቀን ድረስ  መመዝገብ ይገባቸዋል።

የአሁን የPreK ተማሪዎች አምስቱን ስሜቶች ማሰስ ላይ ትኩረት ይሰጣሉ። ከK-4 ክፍል ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በ Camp Invention ካሪኩለምን በመጠቀም STEMን መማር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ተማሪዎች መተማመን እና ጽናትን ያገኛሉ፣ የራሳቸውን የSTEM ክህሎቶች ይገነባሉ እና እንደCatching Air፣ Mimic Bot እና “Fair Games” የሂሳብ በአል የመሳሰሉ የትብብር እና የፈጠራ የችግር መፍቻ እንቅስቃሴዎች በኩል የንባብ ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ። ወጣት ምሁራን ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ የሰመር ትምህርት ፕሮግራምን ይቀላቀላሉ እና በካምፕ ፈጠራ ካሪኩለም ውስጥ ይሳተፋሉ።

የዚህ አመት የሙያ አሰሳ ካምፕ ጭብጥ ከ 5ኛ-7ኛ ክፍል ያሉ የአሁን ተማሪዎችን በተግባር ላይ፣ ፕሮጀክት ላይ የተመሰረተምህንድስና ሁሉም ቦታ ነው ካሪኩለምን በመጠቀም ያሳትፋል። አምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በሚከተሉት ላይ ይሳተፋሉ ጸሃይዋ አሁን ወጣች፣ የወረርሽኝ ማስጠንቀቂያ፣ ነገሮችን መገለባበጥ እና ገደቡ ሰማይ ነው። ስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች በሚከተሉት ላይ ይሳተፋሉ ምሽቱን ማብራት፣ ከተክሎች እስከ ፕላስቲኮች እና ጊዜው ደርሷል።

ሁለቱም የመጀመሪያ ደረጃ እና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶ ፕሮግራሞች በዕለታዊ መመሪያው ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ደጋፊዎችን እና የእንግሊዝኛ ተማሪ ምርጥ ልምዶችን ይሰጣሉ። የልዩ ትምህርት ድጋፍ አስተማሪዎች ከK-12 ክፍሎች አስተማሪዎችን በቀረበው ካሪኩለም እና ተማሪዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በማገዝ በተለያዩ ምርጥ ልምዶች ይደግፋሉ። Extended School Year (ESY) የልዩ ትምህርት አስተማሪዎች በ ESY ተናጠላዊ የትምህርት ዕቅድ ላይ እንደተዘረዘረው የESY አገልግሎት አጫጭር ሃሳቦችን ያቀርባሉ። የልዩ ትምህርት ጣልቃ ገብነት አስተማሪዎች በተወሰኑ የንባብ እና የሂሳብ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራሞች ተማሪዎችን ያስተምራሉ። በተጨማሪም ሁሉም የሰመር ትምህርት ፕሮግራሞች በሚያስፈልጉ የማህበራዊና ስሜታዊ እንዲሁም/ወይም የህክምና ድጋፍ ለተማሪዎች ለመስጠት የመስከ ላይ አማካሪዎች፣ የማህበራዊ ሰራተኞች እና ነርሶች አሏቸው።

ባለሁለት ቋንቋ   የሰመር ቋንቋ አካዳሚ በስፓኒሽ ተናጋሪ ሃገራት ታሪኮች፣ ጂኦግራፊዎች እና አካባቢዎች ጥናት እስከ አሁን ላይ ያሉ የባለሁለት ቋንቋ K-4 ክፍል ተማሪዎች የበለጸጉ ተሞክሮዎችን በሁለቱም የፕሮግራም ቋንቋዎች በማቅረብ ትኩረት ያደርጋሉ። የባለሁለት ቋንቋ የሰመር ብሪጅ ፕሮግራም በአሁኑ ጊዜ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ወደ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ሽግግር ላይ ድጋፍ ለማድረግ እለታዊ ክፍለ ጊዜን ያቀርባል። ይህ ፕሮግራም በGeorge Washington Middle School ከጁላይ 10-20፣ 2023ይካሄዳል።

የሙዚቃ ካምፕ በAlexandria City High School’s King Street Campus ከጁላይ 10-20፣ 2023 ደረጃ የሚመጥን የሙዚቃ መሳሪያ መመሪያን ከ4ኛ-8ኛ ክፍል ለሆኑ ተማሪዎች  ይሰጣል። ሐሙስ ጁላይ 20፣ 2023 ላይ የመጨረሻ ክንውን በማድረግ ካምፑ ይጠናቀቃል። Theatre Camp በGeorge Washington Middle School ከጁን 26-ጁላይ 13፣ 2023 (ማክሰኞ ጁላይ 4፣ 2023 ካምፕ የለም) ከ6ኛ-8ኛ ክፍል ለሆኑ ተማሪዎች መመሪያን ይሰጣል። ተማሪዎች ስለመድረክ ትወና

የመማር እድል ያገኛሉ እንዲሁም ዲዛይን እና ግንባታን፣ መብራትን፣ ድምጽን፣ የመተወኛ ልብሶችን እና ሜክ አፕን ማዘጋጀት የመሳሰሉ በርካታ ቴክኒካዊ የቲያትር አካላትን ይማራሉ።

ለበለጠ መረጃ እና ዝመናዎች የACPS የሰመር ትምህርት 2023 የድር ገጽን ይጎብኙ።

## ለኤፕሪል 20፣ 2023 የት/ቤት ቦርድ ማጠቃለያ



በኤፕሪል 20፣ 2023 በነበረው ስብሰባ ላይ፣ የት/ቤት ቦርዱ የት/ቤት ቦርድ አወቃቀርን ወደ የተዘበራረቀ የስራ ዘመን የመቀየር እድል ላይ ይፋዊ ችሎት አድርጓል (በዚህ የACPS Express ህትመት ላይ ተዛማጅ ጽሑፍ እና የዳሰሳ ጥናትን ይመልከቱ) እንዲሁም በቦርድ ስብሰባ አጀንዳ ላይ የሚከተሉት ርዕሶችን ሸፍኗል፤

- የአማካሪ ኮሚቴው ከSchool Health Advisory Board አስተያየት አግኝቷል።
- የአትሌቲክ ፕሮግራም አዳዲስ ነገሮች።
- ስለ CIP መጠባበቂያ እና ሶስተኛ ሩብ አመት ሪፖርቶች።

እንዲሁም፣ በቦርዱ ስብሰባ ላይ የተጋራ አዲስ ቪዲዮ የት/ቤት ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ Jacinta Greene የእኛን ስትራቴጂያዊ የሃብት አመዳደብ ግብ እና ACPS ለሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊ ውጤት የሚያመጡ ት/ቤቶች እና ክፍሎች የተለያዩ ግብዓቶችን እና ድጋፍን እንደሚሰጥ ያረጉትን ንግግር ያሳያል። ይህ ቪዲዮ የስትራቴጂክ እቅዱን ተልእኮ፣ ራዕይ እና ግቦች ወደ ህይወት ለማምጣት ሰራተኞችን፣ ቤተሰቦችን፣ ተማሪዎችን እና የማህበረሰብ አባላትን የትምህርት ቦርድ ከክፍሉ ጋር እንዴት እንደሚሰራ ውስጣዊ እይታን የሚሰጥ የቅርብ ጊዜ ተከታታይ የት/ቤት ቦርድ ቪንቴቶች ነው።


በዚህ ተከታታይ ውስጥ ያሉ የቀድሞ ቪዲዮዎች የሚያካትቱት:-

- በሂስፓኒክ ወንዶች መካከል በጊዜው የትኩረት አካባቢ በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች የራሳቸው ሙሉ ብቃት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ለከፍተኛ የጥራት መመሪያ እና የተለየ ድጋፍ ቁርጠኛ ስለሆነው ACPS የምትናገረው የት/ቤት ቦርድ አባል ምክትል ሰብሳቢ የሆነችውን Jacinta Greene የያዘ የማርች 31፣ 2023 ቪዲዮ።
- ሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የመግባት እና የመማር ማነቆዎችን የሚቀንሱ ፕሮግራሞች እና ድጋፎች እንዲኖራቸው ለማድረግ ከስልታዊ ግባችን አንፃር በፌብሩዋሪ 16፣ 2023 የት/ቤት ቦርድ አባል Dr. Michelle Rief የተማሪን ተደራሽነት እና ድጋፍ ሲናገሩ የሚያሳይ ቪዲዮ።
- የት/ቤት ቦርድ ሰብሳቢው የሆንችውን Meagan የሚያሳይ የጃንዋሪ 20፣ 2023 ቪዲዮ። ሁሉም ተማሪዎች የከፍተኛ ጥራት መምሪያ መዳረሻ እና ተሳትፎ እንዳላቸው የሚያረጋግጠውን የእኛን የመመሪያ ልህቀት ስትራቴጂያዊ ግብ የሚገልጸው L. Alderton።
- በዲሴምበር 15፣ 2022 የት/ቤት ቦርድ አባል Tammy Ignacio ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚክ ትምህርትን (SEAL) ማገገሚያን የሚያብራራ፣ ከACPS 2022-23 የትኩረት መስኮች አንዱ የሆነው ቪዲዮ።
- የኖቬምበር 10፣ 2022 የት/ቤት ቦርድ አባል የሆነችው Kelly Carmichael Booz ስለ ACPS 2025 ውይይት ያደረገችውን ቪዲዮን ይዟል። ለፍትሃዊነት ለሁሉም ስትራቴጂካዊ ፕላን ብልሃታዊ አሰላለፍ ስትራቴጂያዊ ግብ።
- የኦክቶበር 20፣ 2022 የት/ቤት ቦርድ አባል በሆነው Abdel-Rahman Elnoubi ስለ በጀት ሂደቱን ጥልቅ የሆነ ትንታኔ ያቀረበውን ቪዲዮ ይዟል።

- የሴፕቴምበር 22፣ 2022፣ [የስትራቴጂክ እቅዱን ራዕይ፣ ተልእኮ እና ዋና ዋና እሴቶችን] እና ፍትሃዊነት ለሁሉም 2025 ስትራቴጂክ ፕላን የዘር ፍትሃዊነትን በልቡ አድርጎ እንዴት ተለዋዋጭ እንደሆነ የሚጋራውን የት/ቤት ቦርድ ሰብሳቢ Meagan L. Aldertonን የሚያሳይ ቪዲዮ

ለት/ቤት ቦርድ የስብሰባ አጀንዳዎች እና ሰነዶች፣ [የኤሌክትሮኒክ ት/ቤት ቦርድን] ይጎብኙ። በተጨማሪም ስብሰባዎችን በቀጥታ እንዴት ማየት እና መሳተፍ እንደሚቻል ስላለ መረጃ [የት/ቤት ቦርድ የስብሰባ ድረ ገጽን] መጎብኘት ይችላሉ።

## ኤፕሪል 13፣ 2023፣ የኮቪድ-19 Alexandria COVID-19 የማህበረሰብ ደረጃ




ከኤፕሪል 13፣ 2023 ጀምሮ፣ የAlexandria ከተማ የኮቪድ-19 የማህበረሰብ ደረጃ ዝቅተኛ ነው ሲሆን ባለፉት ሰባት ቀናት 22.58 ኬዞች በ100,000 ግለሰቦች ነው። የበለጠ ለማወቅ [Alexandria የኮቪድ-19 ዳሽቦርድ] ይመልከቱ።

ዳታው ለመጨረሻ ጊዜ የዘመነው በኤፕሪል 13፣ 2023 መሆኑን እባክዎ ልብ ይበሉ። The Centers for Disease Contrssol and Prevention የኮቪድ-19 የማህበረሰብ ደረጃን ለማወቅ ሶስት የምዘና ጥምረቶችን ይመለከታል፦ ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ አዲስ የኮቪድ19 ምዝገባዎች በ100,000 ሰዎች፣ በኮቪድ-19 ታካሚዎች የተያዙ የሰው የታካሚ አልጋዎች ፐርሰንት እና ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ከ100,000 ህዝብ ውስጥ አጠቃላይ አዲስ የኮቪድ-19 ኬዞች።